## የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ባጭሩ

*በእደ ማርያም እጅጉ ረታ*

### መግቢያ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ስንል የኢትዮጵያ ታሪክ ማለት ነው። የአንዲት ሀገርና የአንዲት ቤተ ክርስቲያን ታሪክ በጥምረትና በውህደት የተከናወነውን ታሪክ አጠቃለው ለማስፈር በርካታጸሐፊዎች ጊዜ ወስደው እውቀታቸውን ተጠቅመው ብዙ የደከሙ ቢሆንም፤ እኔም በዘመን ከቀደሙ አባቶች የተቀበልኩትን አደራ በተሟላ መልኩ አዘጋጅቼ እስካቀርብ ድረስ ለመቆያ ያህል ለዚህ ዓምድ በሚጠቅም መልክ በጣም ባጭሩ ቀንጭቤ አቅርቤላችኋለው። ይህ ጽሑፍ በምታነቡበትም ወቅት የጐደለውን እያሟላችሁ፤ ስህተቱን እያረማችሁ በተጨማሪም በአስተያየት መስጫው ላይ እያስፈራችሁ እንድንማማርና የበለጠ ስለ እምነታችንና ስለ ሀገራችን ታሪክ እንድናውቅ የተቻላችሁን እንድታደርጉ አሳስባለሁ።

### ከአኩሱም እስከ ዛጔ ዘመነ መንግሥት

ሃይማኖትን ቀደም ብለው ከተቀበሉት ሀገሮች መኻከል አንዷ ሀገራችን ኢትዮጵያ ነች። የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ክርስትናን የተቀበለው በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን፤ ክርስቶስ ባረገ በዓመቱ ማለትም በ34 ዓ.ም በሐዋርያው በፊልጶስ እጅ ነበር (ሐዋ. 8፤26-40)። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ስለ መንፈስ ቅዱስ መውረድ በተናገረበት ድርሳኑ መንፈስ ቅዱስ በቅድስቲቱ ከተማ በወረደበት ቀን ኢትዮጵያውያንም እንደነበሩ ጽፏል። ይሁን እንጂ የክርስትና እምነት የሀገራችን ዋና እምነት የሆነው በ4ኛው ክፍለ ዘመን በአብርሃ እና አጽብሐ ዘመነ መንግሥት ከ298-336 ነው። በተለይ የክርስትና እምነት በቤተ መንግሥቱ ተቀባይነት ያገኘ ዘንድ ትልቅ አስተዋጽኦ ያደረገው በቀይ ባሕር አካባቢ ተማርከው በምርኮነት ለንጉሠ ነገሥቱ ከተሰጡት የግሪክ ተወላጅ ከሆኑት ወንድማማቾች ፍሬምናጦስና ኤዲሰስና መኻከል በኋላ በኢትዮጵያ ተሹሞ የመጣው ፍሬምናጦስ ወይም ከሣቴ ብርሃን (በ330 ዓ.ም አካባቢ) በመባል የሚታወቀው ነው። ፍሬምናጦስም ተሹሞ ከተመለሰ ጊዜ አንስቶ ከ111 ያላነሱ ግብጻውያን ሊቃነ ጳጳሳት በኢትዮጵያ ተሹመዋል። በተለይ ደግሞ በሀገራችን የክርስትና እምነት በሌሎች ሀገሮች እንደታየው አለምን ደም መፍሰስ በፍጥነት ለመስፋፋት ትልቅ አስተዋፅኦ ያደረገው እምነቱ በቤተ መንግሥቱ ተቀባይነት ማግኘቱ ነው። ፍሬምናጦስ ቀሳዉስትንና ዲያቆናትን በመሾም መንፈሳዊ ተልእኮውን ሲያካሄድ ቆይቶ ዐረፈ። ፍሬምናጦስ በግሪክና በሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ የተባለ ሲሆን፣ በዓሉም በግሪክ ቤተ ክርስቲያን እ.አ.አ በኅዳር 30 ቀን ሲከበር በሮማ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ እ.አ.አ በጥቅምት 27 ይከበራል። ሾማ በላከችው የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ግን የሚታሰብበት ቀን የለውም።

ፍሬምናጦስ ካረፈ በኋላ ሁለተኛው የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ሚናስ ተሹሞ መጣ። ይህ በእንዲህ እያለ በእልአሜዳ ዘመነ መንግሥት በ472 ዓ.ም አካባቢ የሁለት ባሕርይን እምነት አንቀበልም ያሉ 9ኝ የቤተክርስቲያን አባቶች ወይም ተስዐቱ ቅዱሳን በመባል የሚታወቁት ከቊስጥንጥንያ አሁን ቱርክ ከሚባለው፣ ከሶርያና ከሌሎች የሮማ ግዛቶች ወደ ኢትዮጵያ ተሰደው መጡ። የእነዚህ አባቶች ወደ ኢትዮጵያ መምጣት ለታላላቅ ገዳማት መመሥረት፣ ብዙ የቅዱሳት መጻሕፍት ወደ ግእዝ መተርጐም፣ የጣዖት አምልኮ እንዲቀርና የክርስትና እምነት ወደ ሌሎች የኢትዮጵያ ግዛቶች እንዲያውም አልፎ ተርፎ ከቀይ ባሕር ባሻገር ወደ የመን እንዲሰፋፋ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል።

በዐፄ ካሌብ ዘመነ መንግሥት ክርስትና እየተስፋፋ በሄደበት ዘመን፣ ከቀይ ባሕር ባሻገር ባለው የኢትዮጵያ ግዛት በነበረው ደቡብ ዐረብ ክፍል (የመን) በአካባቢው የሚኖሩ አይሁዳውያን በዱዋ ኑዋስ መሪነት ዛፋር ላይ የሚገኙትን ክርስቲያኖች ተሰብስበው በቤተ ክርስቲያን ሲጸልዩ እንዳሉ ካቃጠሉአቸው በኋላ ወደ ናግራን በማምራት በዚያ ከሰፈረው የኢትዮጵያ ጦር ገጥመው ከተማውን ለመያዝ ባይችሉም ከፍተኛ ጉዳት አደረሱ። ይህ ዜናም በወቅቱ ነግሠው ከነበሩት ከዐፄ ካሌብ ዘንድ እንደተሰማ ለጦርነት ዝግጅት ተጀመረ።

በ516ዓ.ም አካባቢ 120,000 ሺህ የሚሆን ጦር ይዘው ለንግድ መጥተው የነበሩ በጠቅላላው ወደ 230 በሚደርሱ መርከቦች አሰባስበው ከአዱሊስ ወደብ አካባቢ ተነሥተው ወደ ናግራን ዘመቱ። ጦርነቱን ቢያሸንፉም ዱዋ ኑዋስ አመለጠ። ካሌብም በዛፋር የፈረሱትን አብያተ ክርስቲያናት እንደገና አሠርተው፣ በቂ ጦር ትተው ወደ አኩሱም ተመለሱ። ይሁን እንጂ የንጉሡን መመለስ የሰማው ዱዋ ኑዋስ እንደገና እየወረረ በዚያ በሰፈረው የኢትዮጵያ ጦር ላይ አደጋ ማድረስ ጀመረ። በዚህ የተነሣ ዐፄ ካሌብ ከ2 ዓመት በኋላ ተመልሰው ወደ የመን ዘመቱ። ዱዋ ኑዋስ እንደለመደው የኢትዮጵያ ጦር ከባህር እን

ዳስ ወደ መሬት እንዳይጠጋ ሲዋጋ በጀርባ በየመን የሰፈረው ጦር ከቦት ማምለጫ ስላሳጣው ከመማረክ ብሎ ወደ ባህሩ ገብቶ ከብዙ ሰራዊቱ ጋር ሞተ። ከዚያም ዛፋር በሚገኘው የቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን በተካሄደው ሥርዓት አብርሃ የተባለውን መሪ አድርገው ሾመው 5000 ጦር በየመን ትተው ከ33 ቀናት በኋላ ወደ አኩሱም ተመለሱ። ዐፄ ካሌብ ከድሉ መልስ በኋላ መንግሥታቸውን ትተው ፣ ሥርዓተ ንግሥና የተቀዳጁበትን ዘውድ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተቀበረበት በጎልጎታ (ኢየሩሳሌም) እንዲቀመጥላቸው ልከው፣ የቀረ ዘመናቸውን በብሕትውና በአባ ጴንጤሌዎን ገዳም ኖረው በ70 ዓመታቸው ዐረፉ።እኝህ ታላቅ ንጉሥ በየመን ሥቃይ ለደረሰባቸው ክርስቲያኖች በመድረሳቸውና የቀረ ዘመናቸውን በፍጹም ምናኔ በማሳለፋቸው፣ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እንዲሁም በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ተብለዋል። በግሪክ ቤተ ክርስቲያንም የናግራን ሰማዕታት ዕለት በሚከበርበት ቀን ዐፄ ካሌብም ታስበው ይውላሉ። በዓሉም እንደ አውሮጳውያኑ አቈጣጠር በየዓመቱ ጥቅምት 27 ቀን ነው።

ከዐፄ ካሌብ በኋላ የነገሡት ዐፄ ገብረ መስቀል (527-541 ዓ.ም) ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን ያሳነጹ ሲሆን ከነዚህም መካከል በየሃ የሠሩት የቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን፣ እስከ አሁን በጥሩ ሁኔታ የሚገኘው የደብረዳሞ ገዳም እና በቤጌምድር ውስጥ ጋይንት የሚገኘው የዙር አምባ ቤተ ክርስቲያን እና ጣና ቂርቆስ ጥቂቶቹ ናቸው። ለገዳማቱም ከፍ ያለ ንዋየ ቅድሳትና የሚተዳደሩበት መሬት ሰጥተዋል። ከዐፄ ገብረ መስቀል በፊት ነገሥታቱ የንግሥ ሥርዓታቸውን የሚያደርጉት ሕዝብ በተሰበሰበበት ቦታ ነበር። ነገር ግን ዐፄ ገብረ መስቀል ከሳቸው ዘመነ መንግሥት ጀምሮ ሥርዓተ ንግሡ በቤተክርስቲያን እንዲሆን ሥርዓት የተከሉና እስከ መጨረሻው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ድረስ ይህ ሥርዓት ተጠብቆ ቆይቷል።

በዐፄ ገብረ መስቀል ዘመን ታላቁ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዜማ ደራሲ የሆነው ቅዱስ ያሬድም የተገኘበትና ከተስዐቱ ቅዱሳን ዘንድ ፣በተለይ ከአባ አረጋዊ የቤተ ክርስቲያን ትምህርቱን እንደተማረ ይነገራል። ቅዱስ ያሬድም እስካሁን ድረስ የምንጠቀምበትን አምስቱ ጸዋትወ ዜማዎች በተለያዩ ጊዜያት የደረሰ ባለውለታችን ነው። የዜማዎቹ ይዘት ሲታይ፣ ቅዱስ ያሬድ ጥልቅ የሆነ የብሉይ፣ የአዲስ ኪዳን እንዲሁም የልዩ ልዩ መጻሕፍት ዕውቀት እንደነበረው ለመረዳት ይቻላል። ዐፄ ገብረ መስቀል ከቅዱስ ያሬድ ጋር በመሆን የሆሣዕና ዕለት አንድ ሰው በአህያ ላይ ተቀምጦ በቤተ ክርስቲያን ዙሪያ መዞርን ሥርዐት የተከሉ ናቸው።

የክርስትና እምነት ከዘመን ወደ ዘመን እየተስፋፋ ቢሄድም፣ እንቅፋት ማጋጠሙ አልቀረም። ይኸውም የሆነው ዮዲት ወይም ጉዲት በመባል የምትታወቀው (ከ842 - 882 ዓ.ም) ከፈላሻ ወገን የምትሆን፣ በወቅቱ ነግሦ የነበረውን አንበሳውድምንበ ጦርነት አሸንፋ በአምባ ገነንነት ከነገሠች በኋላ ነው። ጉዲት ፀረ ክርስቲያን ስለነበረች ትልልቅ የትምህርት ማዕከል የነበሩትን ገዳማት፣ አብያተ ክርስቲያናት፣ ታሪካዊ ሐውልቶች ፣ መጻሕፍት በማቃጠልና በማጥፋት፣ እንዲሁም ካህናቱን በመግደል በማሳደዷ ቀደም ብሎ በነበሩት ዘመናት ይካሄድ እንደነበረው ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያዊ ተልዕኮዋን ለመወጣት አስቸጋሪ ሆኖባታል።ጉዲትም ለ40 ዘመን እንዲህ ዓይነት ጥፋት ስታካሂድ ቈይታ ስትሞት በስደት በሌላው የኢትዮጵያ ክፍል የነበረው አንበሳውድም መንበረ መንግሥቱን (ከ882 - 902 ዓ.ም) ይዞ በርስዋ ዘመን የጠፉትንገዳማት፣ አብያተ ክርስቲያናት እንዲሠሩ አደረገ። የጉዲት ጥፋት ሳያንስ፣ በዚሁ ዘመን የእስልምና እምነት መስፋፋት የጀመረበት በመሆኑ ለ40 ዘመንም በጉዲት የጭካኔ ተግባር ብዙ ካህናት በማለቃቸው እና ሌሎችን ለመሾም አብያተ ክርስቲያናትን ለመባረክ ጳጳስ ማስመጣት ቢያስፈልግም ቀላል አልነበረም። ስለዚህ ይህ ወቅት የቤተ ክርስቲያን ዕድገት የተገታበት ነበር። ይኸም ሆኖ አባቶቻችን ይህ የጨለማ ዘመን አልፎ ተመልሶ የተስፋው ብርሃን እንዲያንሰራራ የተቻላቸውን ሁሉ ከማድረግ አልተቈጠቡም ነበር።አንበሳውድም ካረፈ በኋላ ልጁ ድልነዓድ (ከ902 - 912 ዓ.ም) ነገሠ።

## የዛጔ ዘመነ መንግሥት

በ912 ዓ.ም አካባቢ መራ ተክለ ሃይማኖት በትረ መንግሥቱን በኃይል ወስዶ፣ መንበረ መንግሥቱን ከአኵሱም ወደላስታ አዛውሮ ስመ መንግሥቱንም ዛጔ ብሎ ነገሠ። በዚህም የተነሣ የዛጔ ሥርወ መንግሥት ተብሎ ሲታወቅ ከዛጔ ጋር 11 የርሱ ወገኖች ነግሠዋል ፤ ይኸም ከ912 እስከ 1245 ነው። እነዚህ ነገሥታትም የክርስትና እምነት ይበልጥ ይስፋፋ ዘንድ ጳጳሳትን ከግብጽ እንዲመጡ በማስደረግ ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል። ከዚያም አልፎ ሀገራችን ሰፊ በመሆኗ ተጨማሪ ጳጳሳት እንዲላኩና ኢትዮጵያውያንም ለዚህ ደረጃ እንዲበቁ ጥያቄ ከማቅረብ አልተቆጠቡም።

ከዛጔዌ ሥርወ መንግሥት ከነገሡት መኻከል በጣም ታዋቂ የነበሩት ይምርሃነ ክርስቶስ (ከ1077 - 1117 ዓ.ም) እና ላሊበላ (ከ1157 - 1197 ዓ.ም) ናቸው። ይምርሃነ ክርስቶስ አስማትና ጥንቆላ እንዲሁም አንድ ሰው ከአንድ በላይ እንዳያገባ እንደ መጽሐፍ ቅዱሱ ቃል ራሱን አርአያ በማድረግ ሕግ የደነገገ ነው። በተለይ ላሊበላ በአንድ አካባቢ ያነጻቸው እስካሁን የሚታዩት ከቋጥኝ ተፈልፍለው የተሠሩት 11 አብያተ ክርስቲያናት ዓይነተኛ ምስክሮች ናቸው። በሌሎች የኢትዮጵያ ግዛቶች

ም ተመሳሳይ አብያተ ክርስቲያናት አሳንጿል። ላሊበላ ያሠራቸው እነዚህ ድንቅ የሆኑ ሕንጻዎች በአሁኑ ወቅት ዓለም አቀፍ ታሪካዊ ቅርሶች ተብለው ተመዝግበዋል።

ለትልልቅ ገዳማት መመሥረትና የክርስትና እምነት ከዚያ ቀደም ባልደረሰባቸው ቦታዎች እንዲዳረሱ ትልቅ አስተዋጽኦ ያደረጉት ኢየሱስ ሞዐ እና በኋላ ቅዱስ የተባሉት ተክለ ሃይማኖት የመጀመሪያ ስማቸው ፍስሐ ጽዮን የተወለዱት በዚሁ በበዛጌ ሥርወ መንግሥት ጊዜ ነው። በዐፄ ነአኩቶ ለአብ ዘመነ መንግሥት ለረጅም ጊዜ ጳጳስ ካለመኖሩ የተነሣ የካህናት ቁጥር በጣም እያነሰ በመምጣቱ ንጉሡ ካህናቱን ሰብስበው ጳጳስ እስኪመጣምን ማድረግ እንዳለባቸው ከተወያዩ በኋላ ከመሐከላቸው አቡነ ተክለ ሃይማኖት በጊዜያዊነት ጳጳስ እንዲሆኑ አደረጓቸው። አቡነ ተክለ ሃይማኖትና ኢየሱስ ሞዐ (1203-1284 ዓ.ም) ከሐዋርያዊ ተልዕኮአቸው ባሻገር ሥርወመንግሥቱ ከዛጌ ወደ ሰሎሞናዊ በሰላም እንዲሻገር ትልቅ አስተዋጽኦ አድርገዋል። የዛጌ ሥርወ መንግሥትም ለ333ዓመታት ከቈየ በኋላ ሥልጣኑን ይኩኖ አምላክ ጨበጠ፤ መቀመጫውንም በሸዋ ተጉለት አደረገ (1263-1278 ዓ.ም)።

## ከይኩኖ አምላክ እስከ ዘመነ መሳፍንት

እንደ ቀደምት ነገሥታቱ ሁሉ፣ ይኩኖ አምላክ የክርስትና እምነት እንዲስፋፋ ከመጣር አልቦዘኑም። አቡነ ተክለ ሃይማኖት ከዛጌ ሥርወ መንግሥት ወደ ሰሎሞናዊው መንግሥት መንበረ መንግሥቱ እንዲዛወር ያደረጉ ቢሆንም፣ ይኩኖ አምላክ ሀገሪቷን ሙሉ በሙሉ ለመቈጣጠር ይችሉ ዘንድ የግድ ጳጳስ አስፈልጓቸው ነበር፤ ምክንያቱም የእሳቸው ሹመት ጊዜያዊ ነበርና። ይኩኖ አምላክ ጳጳስ እንዲላክላቸው ላቀረቡት ጥያቄ መልስ ባለማግኘታቸው ፤ለየመኑ ኢማም ደብዳቤ በመጻፍ ጥያቄው በቶሎ ምላሽ  እንዲያገኝ የተቻለውን ሁሉ እንዲያደርግላቸው ጠይቀው ነበር። ይሁን እንጂ ለጠየቁት መልስ ሳያገኙ ቀርተዋል። ይኩኖ አምላክ የላሊበላን ፈለግ በመከተል ላስታ ውስጥ አብያተ ክርስቲያናት ማሳነጽ ቀጠሉ። በተለይ ከሮሃ ብዙ ሳይርቅ ያሠሩት የገነተ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ሕንጻውም ሆነ በውስጡ የሚገኙት ሥዕላት ድንቅ ናቸው። በውስጡም እንዲህ የሚል ጽሑፍ ተቀርጿል «በአኮቴተ እግዚአብሔር ዘሐነጽኩ አነ ይኩኖ አምላክ ዘአንገሠኒ እግዚአብሔር በፈቃዱናሕዮ በክርስቶስ አቡየ ላዕከ ኮነኒ ወአሐንጽ ቤተ ዛቲ ቤተ ክርስቲያን በስመ መጣዕ ይምሐረኒ እግዚአብሔር በመንግሥተ ሰማያት ምስለ አበዋንዮ መሐሪ አምላክ አሜን።»

በመኻል ሌሎችም ነገሥታት የነገሡ ቢሆንም ቀጥሎ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ትልቅ ታሪክ ሠርቶ ያለፉ መሪ ታላቁ ዐፄ ዐምደ ጽዮን ናቸው (ከ1307- 1337 ዓ.ም)። በተዋጊነት ችሎታቸው የታወቁት ዐፄ ዐምደ ጽዮን ሥልጣኑን ከተረከቡ አንስቶ የንግዱን እንቅስቃሴውን እና የኢትዮጵያን ዳር ድንበርና ለመቆጣጠር ቻሉ። በትረ መንግሥቱን ከጨበጡ በኋላ የአባትህን ሚስት ወይም እንጀራ እናትህን ማግባት አይገባህም በማለት በንጉሡና በአቡነ ፊልጶስ እንዲሁም ከሌሎችም ካህናት ጋር በተፈጠረው ችግር ቅራኔ ቢፈጠርም፣ ውሎ ዐድሮ ከታሪክ እንደታየው የሀገርን ድንበር ከማጠናከር ባሻገር መጻሕፍት እንዲጻፉ አብያተ ክርስቲያናት ቀደም ብለው ባልተሠሩባቸው ቦታዎች እንዲተከሉ ከፍ ያለ አስተዋጽኦ ያደረጉ መሪ ናቸው።

ምንም እንኳን አንዳንዶች ክብረ ነገሥት በዛጌ ሥርወ መንግሥት የተጻፈ ነው ቢሉም፣ ዐፄ ዐምደ ጽዮን በዘመነ መንግሥታቸው የቀደሙት ነገሥታት ታሪክን ወይም ክብረ ነገሥት በመባል የሚታወቀው እንዲጻፍ ያደረጉና ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የነገሥታቱ ዜና መዋዕል የመጻፍ ልምድ ሥርዓትን የተከሉ ናቸው።  ዐፄ ዐምደ ጽዮን ከሀገር ውጭ ኢየሩሳሌም በቅዱሳን መካናት ለሚገኙት ኢትዮጵያውያን አባቶችን በሚቻላቸው ከመርዳት አልተቆጠቡም። በወቅቱ ለእነዚህ አባቶች የላኩት መጽሐፍ በአሁኑ ጊዜ በቫቲካን መጻሕፍት ቤት ይገኛል። በመጽሐፉም ገጽ መጨረሻ ላይ «ዘንተ መጽሐፈ ነገሥት በፃዕኩ አነ ዐምደ ጽዮን ንጉሥ ወስመ መንግሥትየ ገብረ መስቀል ንጉሠ ኢትዮጵያ ለእግዝእትየ ማርያም ለኢየሩሳሌም ከመ ታስተሠሪሊተ ኃበ ፍቁር ወልዳ አመ ይመጽእ በስብሐቲሁ ከመ ይረሲ ማኅደርየ ምስለ ቅዱሳኒሁ ወኅሩያኒሁ ለዓለመ ዓለም አሜን» ይልና ቀጥሎም «ኦ አበውየ ወአኃውየ እለ አንበብክምዋ ለዛቲ መጽሐፍ ዝክሩኒ በጸሎትክሙ ከመ ይምሐረኒ ወይሣህለኒ..... ....» የሚል አለበት።

በዚሁ ባ14ኛው ክፍለ ዘመን በዐፄ ዳዊት 1ኛ፣ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት ግማደ መስቀል ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ፣ በመጨረሻም አሁን ባለበት በወሎ ክፍለ ሀገር በአምባ ግሼን ተቀምጧል።

ቀጥሎም የነገሡት ዐፄ ቴዎድሮስ 1ኛ (1403-1406 ዓ.ም) ምንም እንኳን ላጭር ጊዜ ቢነግሡም በዘመኑ ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን ያሳነጹ፣ ብዙ ትልልቅ መጻሕፍትን ያስጻፉ ሲሆን፤ እነዚህም መጻሕፍት ከጥፋት ተርፈው በአሁኑ ወቅት በሀገራችንና በአውሮጳውያን ሙዚየሞች ይገኛሉ።

ከእነዚህ ቀጥሎ የተነሡት ዕውቅ ንጉሠ ነገሥት ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ነበሩ (1426-1460 ዓ.ም)። ዘመነ መንግሥታቸውም ወርቃማው የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ ዘመን በመባል ይታወቃል። ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ መንበረ መንግሥታቸውን ከተጉለት ወደ ደብረ ብርሃን አዛወሩ። በዘመነ መንግሥታቸው በጣም ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን ያሳነጹ፣ ብዙ መጻሕፍት የተጻፉበት ራሳቸው

ብቻ 8 መጻሕፍት ጽፈዋል። ይህ ወቅት እንደ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ የመሰሉ አባቶች የተነሡበት ነበር። አባ ጊዮርጊስ መ ጽሐፈ ምስጢርን፤ አርጋኖን ድንግልንና የሌሊት ጸሎት ሰዓታትን ጽፈዋል። በዚህ ወቅት ስለ ቅዱሳን፣ ስለ ቤተክርስቲያን ታሪክ ፣ ስለ አይሁድ ታሪክ፣ የተለያዩ መጻሕፍት ተተርጉመዋል ፤ ከእነዚህም አንዱ ተአምረ ማርያም ነው። ዐፄ ዘርዐ ያዕ ቆብ ሀገራቸውን አጠናክሮ ለመግዛት ዜጎቹን ባንድ እምነት ሥር ማምጣት እንዳለባቸው ስላመኑና ክርስትና እንዲስፋፋ ካህ ናት እምነትንና ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን ለምእመናን በሰንበትና በዐበይት በዓላት ቀን እንዲያስተምሩ ጥብቅ ትዕዛዝ አስተ ላልፈው ነበር። ዓላማቸውንም ለማሳካት ይረዳቸው ዘንድ ከዚያ ቀደም ሆኖ የማያውቀውን ባንድ ጊዜ 3 ጳጳሳት ለማስመጣ ት ችለው ነበር። በኢየሩሳሌም ለሚገኙት ኢትዮጵያውያን አባቶች ለምግብና ለልብስ መግዣ እንዲሆናቸው ከዘይላ ወደብ ከሚገኘው ቀረጥ በየሁለት ዓመቱ 100 ወቂት ወርቅ እንዲሁም ብዙ መጻሕፍትን ከሸኚ ደብዳቤ ጋር ልከውላቸዋል።

የመንፈሳዊ ትምህርት ቤቶችም የበለጠ እንዲስፋፉ ከፍ ያለ ጥረት አድርገዋል። ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ለክርስትና ሃይማኖት ፍ ጹም ቀናኢ ስለነበሩ ለጣዖት መስገድ የሞት ቅጣት እንደሚያስከትል ዐወጀው፤ ይህን ሕግ ከመጣሳቸው የተነሣም ከተገደሉ ት መሀከል የእሳቸው 8 ልጆቻቸው ናቸው፤ ሁሉ ከሕግ በታች ነውና። በዚሁ በዘርዐ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት በ1441 በ ጣሊያን ፍሎረንስ በተካሄደው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ኢትዮጵያ እንድትገኝ ለቀረበላት ግብዣ በኢየሩሳሌም ከ ሚገኙት ኢትዮጵያውያን አባቶቻችን መኻከል በገዳሙ አበምኔት አማካኝነት 2 ተወክለው ተገኝተዋል። ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ በመንፈሳዊውም ይሁን በሥጋዊው አስተዳደር ከፍተኛ ችሎታ ያሳዩ ታላቅ መሪ ናቸው።

ከእሳቸው በኋላ የነገሡት ልጃቸው በእደ ማርያም (1460-1470 ዓ.ም) ሲሆኑ የአባታቸውን ፈለግ በመከተል ብዙ አብያተ ክ ርስቲያናትን ያሳነጹና ብዙ መጻሕፍት እንዲጻፍ ያደረጉና ራሳቸው መልክአ ሚካኤልንና መልክአ ቁርባንን ደርሰዋል። በተለ ይ በዘመኑ አትሮንስ ማርያም የምትባለውን ቤተክርስቲያን አሠርተው፣ ውስጧን በወርቅና በዕንቍ አንቆጥቄጦ እንዳሠሯት በተጨማሪም በጣሊያኑ (ቬኒሺያኑ) ተወላጅ ብራንካ ሊዮን የምስለ ፍቁር ወልዳን ሥዕል እንዲሣል አድርገዋል። እንዲሁም ከሳቸው ቀድመው ያረፉትን የ22 ነገሥታት እንዲሁም በልጅነት የዳዊት መዝሙርን ያስተማራቸውን የመምህራቸውን የተ ክለ ኢየሱስን ዐፅም ከተቀበሩበት አስወጥተው በአትሮንስ ማርያም ቤተ ክርስቲያን እንደገና እንዲያርፍ አድርገዋል።

ተከታትለው ከነገሡት የዐፄ በእደ ማርያም ልጆች መኻከል ዐፄ እስክንድር (1470-1687) በዘመነ መንግሥታቸው አብያተ ክ ርስቲያናትን እንዲታነጹ ከማድረግ ሌላ ኦርጋን አባታቸው ባሳነጹት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በአንድ የጣሊያን ተወላጅ እንዲ ሠራ አድርገዋል። ይሁን እንጂ ባለሙያ ባለመኖሩ በመሳሪያው የመጠቀም ልምድ አልቀጠለም። ከሳቸው ቀጥሎ የነገሡት ወንድማቸው ዐፄ ናዖድ (1487- 1500 ዓ.ም) ጥልቅ የሆነ የሐዲስና የብሉይ ዕውቀት እንደነበራቸው ከተቀኟቸው ቅኔዎች መ ረዳት ይቻላል። እንደ ቀደምት አባቶቻቸው አብያተ ክርስቲያናትን እንዲታነጹ ፤ እንዲሁም መጻሕፍት እንዲተረጐሙ ከ ማድረግ ዐልፎ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ በቤተ ክርስቲያን እስከ አሁን የሚጸለይበትን መልክአ ማርያምን ደርሰዋል።

ዐፄ ናዖድ ካረፉ በኋላ ልጃቸው ዐፄ ልብነ ድንግል ከ1500- 1533 ዓ.ም ነግሠዋል። ዐፄ ልብነ ድንግል እንደ ነገሡ አካባቢ መጻሕፍት ከግሪክኛ እና ከዐረብኛ ወደ ግእዝ እንዲተረጐም እንዲሁም ከዚያ በፊት ከተሠሩት የበለጡ ትልልቅ አብያተ ክ ርስቲያናት እንዲታነጽ አድርገዋል። በወቅቱ ከተተረጐሙት መጻሕፍት መኻከል የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ወደ ዕብራውያን ሰዎች አንድምታ እና የአራቱ ወንጌላት አንድምታ ይገኝበታል። ዐፄ ልብነ ድንግል ለኖኅ ሓመሩን ፣የእመቤታችንን ስብሐ ተ ፍቁር፣ተፈሥሒ ማርያምን፣ ለአዳም ፋሲካሁ፣አ ርጎርጎተ ሕሊናን የተባለው እንደደረሱት ይነገራል። ከ1523-1535 በኢ ትዮጵያ ታሪክ ውስጥ አስከፊውና ብዙ የታሪክ ቅርሶች፣መጻሕፍት በቱርክ መንግሥት ረዳትነት ከምሥራቁ የኢትዮጵያ ክፍ ል በተነሣው ግራኝ አህመድ ወራሪነት የወደሙበት የጠፉበት ዘመን ነበር። እነዚያ ከፍተኛ አድናቆትን ያተረፉ በወርቅ፣ በ ዕንቍ ተለብጠው የተሠሩ ታላላቅ አብያተ ክርስቲያናት በውስጣቸው ያለው ወርቅ የታቸለው ያህል ከተወሰደ በኋላ፣ በእሳ ት ጋይተዋል። በዚያ የመከራ ወቅት በሰይፍ ተገደው ብዙ ክርስቲያኖች ወደ እስልምና ሃይማኖት ገብተዋል።

ከዐፄ ልብነ ድንግል በኋላ የነገሡት ልጃቸው ዐፄ ገላውዴዎስ (1533- 1551 ዓ.ም) በጦርነት የተጐዳችውን ሀገር ተረክበው ከፖርቱጋል መንግሥት ከተላኩላቸው ወታደሮች ጋር በመሆን፣ የግራኝ አህመድን ጦር እያሳደዱ ድል ማድረግ ጀመሩ ፤ በ 1535 ዓ.ም ግራኝ በጦርነቱ ላይ ተገደለ። ዐፄ ገላውዴዎስም እየተከታተሉ የቀሩትን የግራኝ ተከታዮች ድል እያደረጉ አብያ ተ ክርስቲያናት እንዲታነጹ፣ ወደ እስልምና የገቡ ወደ እምነታቸው እንዲመለሱ በሚጥሩበት ወቅት ለዕርዳታ ከመጡት የ ፖርቱጋል ዜጐች ጋር መግባባት ተቸግረው ነበር። የችግሩ ዋናው መንሥኤ የነበረው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ወደ ሮም ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን እንድትለወጥ መጠየቁ ነበር። ምንም ዓይነት ግፊት ቢበዛባቸው ስለተደረገላቸው ርዳታ በሌላ ይ ከፍላሉ እንጂ ከሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ጋር እንደማይተባበሩ ገልጸው፣ ስለ እምነታቸው መግለጫ አውጥተው የግ ብጽን ቤተ ክርስቲያን ብቻ እንደሚቀበሉ አሳውቀዋል። እነዚህ ከፖርቱጋል የመጡ ካቶሊኮች ለጊዜው የተውት ቢመስሉም ፣ ዐፄ ገላውዴዎስ እንደ አባቶቻቸው ካንቀላፉ በኋላ በዐፄ ሚናስ ዘመነ መንግሥት ሆነ ከሳቸው በኋላ፣ መንበረ መንግሥቱ ወደ ጎንደር ተዛውሮ ዐፄ ፋሲል እስከ ነገሡበት (1623 -1659 ዓ.ም) ድረስ በፈጠሩት የሃይማኖት ችግር፣ ለብዙ ሺህ ኢት ዮጵያውያን ደም መፍሰስ፣ የሃይማኖት ክርክር ፣ መከፋፈል በተለይ ቅብዐትና ጸጋ የሚል የካቶሊክ ሃይማኖት አስተምረው

ለተከታዮቹ ዓመታት ለተፈጠሩት ችግሮች ምክንያት ሆነዋል። ዐፄ ፋሲል ከነገሡ በኋላ ካቶሊኮቹን በሙሉ ከሀገር እንዲ
ወጡ አድርገዋል። ሆኖም ካቶሊኮቹ ዘርተውት የሄዱት የቅብዐትና የጸጋ ትምህርት ዐፄ ፋሲል ዐርፈው ከእርሳቸው በኋላ
በተነሡት በሌሎቹ ነገሥታት ዘመነ መንግሥት ጠንቁ እየቀጠለ ለብዙ ዘመናት ለክርክርና ደም መፍሰስ ምክንያት ሆኗል።

ከዐፄ ሚናስ ቀጥሎ የነገሡት ዐፄ ሠርፀ ድንግል መቀመጫቸውን በጎንደር አድርገው መግዛት ጀመሩ (1556-1590 ዓ.ም)። ከ
ግራኝ ጥፋት በኋላ ቅዱስ ያሬድ የደረሰው መጽሐፈ ድጓ ለረጅም ጊዜ ጠፍቶ በዘመነ መንግሥታቸው በጎንደር ክፍለ ሀገር
በቤተልሔም ስለተገኘ፣ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የድጓ ተማሪ የመጨረሻው ማስመስከሪያው እዚያው እንዲሆን ተወሰነ።

በጎንደር ከነገሡት ከታወቁ ነገሥታት መኻከል ሌላው ዐፄ ኢያሱ አድያም ሰገድ (1674-1698) ሲሆኑ፣ በሳቸው ዘመን በጎን
ደር ያሠሩት የደብረ ብርሃን ሥላሴ ውስጡ ጠቅላላ በሥዕል የተዋበና እስካሁን ድረስ የሚታይ ነው። በዘመነ መንግሥታቸ
ውም በጎንደር ቤተ መንግሥቱ አካባቢ ብዙ የዜማ፣ የቅኔ ትምህርት ቤቶች እንዲቋቋም አድርገዋል፤ በስተመጨረሻም መን
ግሥታቸውን ትተው ወደ ገዳም ገብተዋል።

ከዐፄ ተክለ ጊዮርጊስ (1772- 1777 ዓ.ም) በኋላ በአንድ ንጉሥ ሥር ትተዳደር የነበረችዉ ኢትዮጵያ ዘመነ መሳፍንት ወደ
ሚባለው ክፍለ ዘመን ተሸጋገረች።

## <u>ከዘመነ መሳፍንት እስከ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ</u>

በዘመነ መሳፍንት ቤተ ክርስቲያን እንደቀደመው ጊዜ፣ በተቀናጀ ሁኔታ በነገሥታቱ መሪነት ተልእኮዋን ለመወጣት ወቅቱ አ
ልፈቀደላትም። ይህ ማለት ደግሞ ፍጹም እንቅስቃሴ አልነበረም ማለት አይደለም። በዘመኑ የነበሩት እነዚህ መሪዎች በተና
ጥል ከውጭ ከነበሩ መሪዎች ጋር ስለ ሀገራቸው ጉዳይ ግንኙነት ያደርጉ ነበር። ከእነዚህም አንዱ ሣህለ ድንግል በዘመነ
መንግሥታቸው በኢየሩሳሌም ይኖሩ የነበሩ ኢትዮጵያውያን አባቶች ይደረስባቸው የነበረውን ችግር አስመልክቶ መፍትሔ እ
ንዲያገኙ በወቅቱ በኢየሩሳሌም ለነበረው ገዢና ለሌሎች የቤተ ክርስቲያናት መሪዎች ደብዳቤ ጽፈዋል።

የሆኖ ሆኖ በዚህ መኻል የቋራው አንበሳ ካሳ በኋላ ስመ መንግሥታቸው ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ (ቴዎድሮስ የግሪክ ቋንቋ
ሲሆን ትርጉሜውም የእግዚአብሔር ስጦታ ማለት ነው) በዘመነ መሳፍንት የተከፋፈለችዋን ኢትዮጵያን ወደ አንድነት ለማ
ምጣት ከፍተኛውን ትግል ጀመሩ። ያለ ዕረፍት ከሀገር ሀገር እየዘመቱ የአንድነትን መንገድ እየጠረጉ በሚያደርጉት ትግል
ወቅት ካህናት ወንጌልን እየዞሩ እንዲሰብኩ፣ ክርስትና ወደ አልደረሰበት የሀገሪቱዋ ግዛት ሐዋርያዊ ተልእኮ እንዲፈጽሙ
ቢያዟቸውም ፈቃደኝነታቸውን ማግኘት አልቻሉም። እሳቸውም የውጭ ሚሽነሪዎችን በሀገራቸው በቂ ካህናት ያሉና ከእነር
ሱ በፊት ደግሞ ኢትዮጵያ የክርስትናን እምነት የተቀበለች በመሆኗ እንዳያስተምሩ ከልክለዋቸው ነበር። ይሁን እንጂ ካህና
ቱ ዐፄ ቴዎድሮስ እንደ ፈለጉት ለሐዋርያዊ ተልእኮ ባለመጣራቸው ፤የውጭ ሚሽነሪዎቹ ፈላሻዎችንና እስላሞቹን ብቻ እን
ዲያስተምሩ፤ ሲያምኑም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እንዲጠመቁ ፈቀዱላቸው። ካህናቱንም ሐዋርያዊ
ተልእኮ የማይፈጽሙ ከሆነ፣ ለአንድ ቤተክርስቲያን ከ5ካህናት በላይ አያስፈልግም፤ ሌሎቻችሁ «አርሳችሁ ብሉ» ብለው
አዘዙ። ይህ ከካህናት ጋር የተጀመረ አለመግባባት ውሎ ዐድሮ ለሥራቸው እንቅፋት ሆኖባቸዋል። የስዊስ ዜጋ የነበረው ኪ
ንዘል በዐፄ ቴዎድሮስ ትዕዛዝ እጅና እግሩ በሰንሰለት ታስሮ ሲሰቃይ ኖሮ በኋላ ተፈቶ ወደ ሀገሩ ሲገባ በጻፈው ማስታወሻ
ላይ በአበሻ ሀገር ላይ እንደ ቴዎድሮስ ፍጹም እግዚአብሔርን የሚፈራ የለም፤ ሲል ምስክርነቱን ሰጥቷል። ዐፄ ቴዎድሮስ
ከውጭ ሚሽነሪዎች ጋር በአንድ ወቅት ሲወያዩ ለምንድን ነው በዓለም ላይ ያለነው እኛ ክርስቲያኖች እንደ እስላሞቹ ሁሉ
አንድ የማንሆነው? በማለት ጠይቀዋቸው ነበር። ዐፄ ቴዎድሮስ እንደ መጽሐፉ ሕግ ለሌሎች አርአያ ለመሆን ሞክረዋል።
ቤተ ክርስቲያን እንድትስፋፋ ለማድረግና ሕዝቡንም በአንድ እምነት ሥር ለማምጣት ቢጥሩም በወቅቱ ከነበሩት ካህናት ት
ብብርን አላገኙም። «የኢትዮጵያ ባል፣ የኢየሩሳሌም እጮኛ» ብለው የሚፎክሩት ቴዎድሮስ፣ በወቅቱ በሀገር ውስጥ ባለባቸ
ው የሥራ ውጥረት በኢየሩሳሌም ለሚገኙት አባቶች ምንም ማድረግ ባይችሉም የእንግሊዝ መንግሥት እንዲንከባከባቸውና
ጉዳያቸውን እንዲያስፈጽምላቸው አድርገዋል። ይህም በዐፄ ቴዎድሮስና እንግሊዞች መኻከል በተፈጠረው አለመግባበት የ
ዲፕሎማቲክ ግንኙነቱ እስኪቋረጥ ቀጥሏል። በኢትዮጵያም የመጀመሪያውን ቤተ መጻሕፍት (ላይብረሪ) በማቋቋም ብዙ የ
ብራና መጻሕፍት ከተለያዩ ታላላቅ ደብሮች መጥተው በዚያ እንዲቀመጡ አደረጉ። የእንግሊዘ ጦር ወደ ኢትዮጵያ እስረኞ
ችን ለማስለቀቅ በዘመተ ጊዜ፣ መቅደላ ላይ የሚገኙትን እነዚህን ብርቅ መጻሕፍትን ዘርፈው ወስደዋል። በአሁኑ ጊዜ እነዚ
ህ ልዩ የሀገር ቅርሶች በብሪቲሽ ቤተ መጻሕፍት ይገኛሉ።

ቀጠል ለእምነታቸው በጣም ተቆርቋሪ የነበሩት ዮሐንስ 4ኛ፣ ዐፄ ቴዎድሮስ የጀመሩትን የኢትዮጵያ አንድነት ማጠናከር ቀ
ጠሉበት። ፍሬምናጦስ ከተሾመበት ጊዜ አንስቶ ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ 3 ጳጳሳት እሲኪያስመጡ ድረስ ኢትዮጵያን ለምታህል ሰ
ፊ ሀገር እየተሾመ ይላክ የነበረው አንድ ጳጳስ ብቻ ነበረ። ከዚያም በኋላ ለተከታዮቹ 5 ክፍለ ዘመናት ያው ከዐፄ ዘርዐ
ያዕቆብ በፊት እንደነበረው አንድ ጳጳስ ብቻ ሲላክ ቆይቶ ነበር፤ በዐፄ ዮሐንስ ግን በዘመነ መንግሥታቸው ከግብጽ 4 ጳጳሳ

ት እንዲመጡ አደረጉ። የክርስትና እምነት እንዲስፋፋ፣ አብያተ ክርስቲያናት እንዲታነጹ ፣ የክርስትና እምነት ተከታዮች እንዲበዙ አደረጉ። ኢትዮጵያ ውስጥ እየተዘዋወሩ የሚያስተምሩ የውጭ ሀገር ሚሲዮኖች ከያሉበት ሰብስበው ምን እየሠሩ እንዳሉ ቢጠይቋቸው «ወንጌልን እየሰበክን ነው አሏቸው።» በሀገሬ የሚሰብኩ በቂ ካህናትና ጳጳሳት አሉኝ። ታዲያ ማንን ልትሰብኩ ትፈልጋላችሁ? ሲሉ ጠየቋቸው። «እነርሱም እስላሞቹንና ፈላሻዎቹ አሉ።» በዚህ ጊዜ ንጉሡም ኧረ ለመሆኑ እንዴት የዐረቡን ሀገር ሁሉአልፋችሁ እዚህ ድረስ መጣችሁ? ብለው ሥራቸው ወይም ዓላማቸው ሌላ እንደሆነ ስላወቁ፣ ከኢትዮጵያ አባረው አስወጧቸው። በዚሁ በዐፄ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት ዐፄ ምኒልክ ጭምር በተገኙበት በቦሩ ሜዳ በተዋሕዶዎችና በጸጉች መኻከል ክርክር ተካሂዶ በዕለቱ ተዋሕዶዎች ረትተው ጉባኤው ተፈጽሟል።

በኢየሩሳሌም በኋላ የኢትዮጵያ ጎዳና ተብሎ በተሰየመው መንገድ ላይ ቤተ ክርስቲያን (ደብረ ገነት ኪዳነ ምህረት) ይታነጽ ዘንድ በጦርነት የተማረከ 6 ሳጥን ወርቅ ወደ ኢየሩሳሌም ላኩ።
ዐፄ ዮሓንስ ካረፉ በኋላ ንጉሠ ነገሥት ተብለው ዘውዱን የጫኑት ዐፄ ምኒልክ፣ ኢትዮጵያን ወደ ከፍተኛ ዕድገት ጐዳና የመሩ ፤ በሕዝብ ዘንድ እምዬ ምኒልክ ተብለው ለመጠራት የበቁ ታላቅ መሪ ናቸው። መንበረ መንግሥታቸውን በእንጦጦ ሲመሠርቱ የእመቤታችንን ቤተ ክርስቲያን ተክለዋል። በተለይ ልዩ ዲፕሎማሲያዊ አመራራቸው በሁሉ ዘንድ አድንቆትን አትርፎላቸዋል። በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳማት የሚኖሩት አባቶች እነዚያን ታሪካዊ የሆኑ ቦታዎች ለተከታይ ትውልድ ለማስተላለፍ ሲጠብቁ የሚበሉት ሆነ የሚለብሱት እያጡ ከአርመን ገዳም በሚሰጣቸው መቁነን ብቻ እየኖሩ ከፍ ያለ ችግር ስለ ደረሰባቸው፣ ሁኔታውን በማጤን ዐፄ ምኒልክ ከባለቤታቸው ከእቴጌ ጣይቱ ጋር በመሆን ቋሚ የሆነ የገቢ ምንጭ እንዲኖራቸው ለማድረግ ቆርጠው ተነሡ። በመጀመሪያ ዐፄ ዮሐንስ አስጀምረውት የነበረውን የደብረ ገነት ኪዳነ ምሕረት እንዲያልቅ ገንዘብ ላኩ። በ1895/6 እቴጌ ጣይቱ በኢየሩሳሌም ለሚኖሩት ኢትዮጵያውያን ቋሚ ገቢ እንዲኖራቸው በማሰብ እዚያው ኢየሩሳሌም ውስጥ መሬት ገዝተው ሕንጻ ተሠርቶ እንዲከራይና ተጨማሪ ሌላ ባለ ሁለት ፎቅ ሕንጻ በዚያው ዓመት በመግዛት አበርክተዋል። በመቀጠልም ዐፄ ምኒልክ ግንቦት14 ቀን 1905 እ.አ.አ በኢየሩሳሌም ለሚኖሩት ኢትዮጵያውያን 200,000 ማርትሬዛ ብር ሰጥተዋል። ይህ ገንዘብ በባንክ ተቀምጦ ከሚገኘው ወለድ ማኅበረሰቡ እንዲጠቀምበት አድርገዋል።
ርዳታቸዉም በዚህ አላበቃም። በዓመቱ ሌላ ሁለት ሕንጻዎችን አሠርተው ለገዳሙ አበርክተዋል። በተጨማሪም ሌላ 100,000 ማርትሬዛ ብር ለገዳሙ እድሳት ለግሰዋል። በኢትዮጵያና በግብጽ መኻከል በዴር ሡልጣን የተነሣውን ችግር በዲፕሎማሲያዊ መንገድ እልባት እንዲገኝለት በማሰብ፣ ዐፄ ምኒልክ መልክተኞችን ወደ ቊስጥንጥንያ (ቱርክ)፣ ኢየሩሳሌም፣ ካይሮና ሩሲያ ከ1883 እስከ 1900 ልከዋል። በ1887/8 ዐፄምኒልክ ደጃዝማች መሸሻወርቁን ስለ ዴር ሡልጣን ጉዳይ እንዲነጋገሩ ወደ ቊስጥንጥንያ ላኩ። በዚያው ዓመት ኒኮላ ቼድቭሬ የተባለ የሩሲያ ዜጋ የኢትዮጵያውያን በኢየሩሳሌም ቅዱሳን ቦታዎች የባለቤትነት መብት የሚያረጋግጡ ሰነዶችን ብዙ ገንዘብ ከፍሎ ከቊስጥንጥንያ ቤተ መዘክር (አርካይቭ) ውስጥ አገኘ። እንደሚታወቀው ሁሉ ከዚያ በቀደሙት ዘመናት ግብጻውያን ተላላፊ በሽታ ገብቷል በሚል ሰበብ ያሉትን መዛግብት ሁሉ ማቃጠላቸው ይታወቃል። ይህ የተገኘው ሰነድ ከቀረበ በኋላ በቊስጥንጥንያ የሚገኘው ፍርድ ቤት አንዱ ቁልፍ ለኢትዮጵያውያን እንዲሰጥ ቢወስንም በወቅቱ ኢየሩሳሌምን ያስተዳደር የነበረው ገዢ ለግብጾቹ ስላደላ የፍርድ ቤቱ ውሳኔ ሳይፈጸም ቀርቷል።

ከዐፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት በኋላ ቀጥለው የነገሡት ንግሥት ዘውዲቱ አባታችው የጀመሩትን አርአያ በመከተል በኢየሩሳሌም በኢትዮጵያ ገዳም ለሚኖሩ አባቶች ደብዳቤ በመጻፍ በማበረታታትና እንዲሁም ሕንጻ በማሠራት ከዚያ በሚገኘው ገቢ ሲሶውን ገዳሙ እንዲጠቀምበት አድርገዋል።

ከ1900ዎቹ መጀመሪያ ጀምሮ ቤተ ክርስቲያናችን በብዙ አቅጣጫ ከፍተኛ እንቅስቃሴ የጀመረችበት ነው። ከነዚህም ዋናዋናዎቹ በግዕዝ ለዘመናት ተጽፈው ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፉ የመጡት መጻሕፍቶቿ ሕዝብ አንብቦ ሊረዳበት በሚችልበት ወደ አማርኛ ቋንቋ እንዲተረጎሙ በ1910 ዓ.ም የመጻሕፍት ንባብና ትርጉም ማሰናጃና የመጻሕፍት ማደራጃ ክፍል በጌታ አለቃ ገብረ መድኅን ተቋቋመ። የትርጉሙም ሥራ 18 በሚሆኑ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ተጀምሮ ቆይቶም ሌሎች አባቶች ተጨምረው ብዙ መጻሕፍት ወደ አማርኛ ለመተረጎም በቅተዋል። የመጀመሪያው የብሉይና የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት በግዕዝና በአማርኛ ነጠላ ትርጓሜ በቁም ጽሕፈት በ1927 ተጽፎ ተዘጋጀ። ይህ በቀጥታ ከግዕዝ ወደ አማርኛ የተተረጎመው መጽሐፍ ቅዱስ ከዕብራይስጡና ከግሪኩ ጋር ተመሳክሮ እንዲዘጋጅ በየካቲት 27 ቀን 1939 10 አባላትን የያዘአንድ የሊቃውንት ጉባኤ ተቋቋመ። ጉባኤውም አስፈላጊውን ጥናት አድርጎ ሐምሌ 12 ቀን 1947 ዓ.ም የአዲስ ኪዳኑን ክፍል በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ታትሞ እንዲወጣ አደረገ። እንዲሁም የብሉይ ኪዳኑ ተከታተሎ በ1952 ዓ.ም እንዲወጣ አድርጓል።

በተጨማሪም ንግሥት ዘውዲቱ በንግሥናቸው ዘመን ለመጀመሪያ ጊዜ በዘመን የቀደሙ ነገሥታት፤ ኢትዮጵያውያን አባቶች ወደ ጵጵስና ደረጃ እንዲደርሱ የተመኙት ከፍጻሜ ደረሰ።

ይኸውም በአልጋ ወራሹና በባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ፣ በራስ ተፈሪ መኮንን ጥረትና ትጋት ከ3 ዓመታት ውይይት በኋላግንቦት 25 ቀን 1921 ዓ.ም 4 ኢትዮጵያውያን አባቶች በካይሮ ተሾሙ።

እነርሱም፤

- አቡነ ጴጥሮስ፣ የወሎ ጳጳስ
- አቡነ አብርሃም፣ የጎጃምና ጎንደር ጳጳስ
- አቡነ ይስሐቅ ፣ የትግሬና የስሜን ጳጳስ
- አቡነ ሚካኤል ፣ የምሥራቅ ኢትዮጵያ ጳጳስ

ሲሆኑ፣ ወደ ኢትዮጵያ ሲመለሱ የበላያቸው ሆነው ግብጻዊው አቡነ ቄርሎስ አብረዋቸው መጡ። በተከታዩ ዓመት የግብጹ ፓትርያርክ አባ ዮሐንስ ኢትዮጵያን ሲጎበኙ፣ ጥር 1 ቀን 1922 ዓ.ም የደብረ ሊባኖስ እጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስን በታዕካ ነገሥት ቤተ ክርስቲያን አቡነ ሳዊሮስ ብለው ሾሟቸው። እነዚህም አባቶች አምስቱ የኢትዮጵያ አእማደ ቤተ ክርስቲያን ተብለው ለመጠራት በቅተዋል።

በሁለተኛው ዓለም ጦርነት ፋሽስት ኢጣሊያ ሀገራችንን በወረረች ጊዜ፣ አቡነ ቄርሎስ ስለ ሀገሪቷ ጉዳይ ለመወያየት ወደ ጣሊያን ሄዱ። አቡነ ቄርሎስም ከኢጣሊያ ሲመለሱ፣ ግብጽ ላይ ከመርከብ ወርደው፣ ወደ ኢትዮጵያ ላለመመለስ ወሰኑ። በዚህ መሐል አቡነ ጴጥሮስ ሐምሌ 22 ቀን 1928 አዲስ አበባ ላይ፤ አቡነ ሚካኤል በሀገረ ስብከታቸው በጎሬ ላይ ሲያስተምሩ ኅዳር 24 ቀን 1929 ስለ ሀገራቸው ክብር በኢጣሊያኖች በጥይት ተደብድበው ተገደሉ።

ፋሽስት ኢጣሊያን ጭፍጨፋዋን በእነዚህ 2 ጳጳሳት አላበቃችም ነገር ግን እንደ ደብረ ሊባኖስ ባሉት ገዳም ውስጥ እንዲሁም በሌሎች ታላላቅ ገዳማት የሚኖሩትን አባቶች ግማሾቹን ከነሕይወታቸው በማቃጠል ግማሾቹን በጥይት ጨፍጭፋለች ።

በተለይ ደግሞ ይህንን ጦር ባርካ የላከችው የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ሌላ ጥቁር ነጥብ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ጥላ አልፋለች። አቡነ ቄርሎስ በዚያው በመቅረታቸው አቡነ አብርሃም በሊቀ ጳጳስነት ደረጃ ቤተ ክርስቲያኒቷን በበላይነት እንዲያስተዳድሩና ሌሎችን ጳጳሳት እንዲሾሙ ኅዳር 21 ቀን 1930 ዓ.ም ተመረጡ። እንደገና የመነመነውን የጳጳሳት ቁጥር ከፍ ለማድረግ ለሐዋርያዊ ተልዕኮ መፋጠን በዚያው ቀን አቡነ አብርሃም ተጨማሪ 6 ጳጳሳትንና ኤጲስ ቆጶሳትን መረጡ። እነርሱም፤

1 / አቡነ ዮሐንስ- የሸዋ ጳጳስ
2 / አቡነ ማርቆስ- የኤርትራ ጳጳስ
3 / አቡነ ሰላማ- የሐረር ጳጳስ
4 / አቡነ ማቴዎስ- የወሎ ጳጳስ
5 / አቡነ ገብርኤል- የጎንደር ጳጳስ
6 / አቡነ ሉቃስ- የወለጋ ኤጲስ ቆጶስ

አቡነ አብርሃም ብዙም ሳይቆዩ በዓመቱ ሐምሌ 14 ቀን 1931 ዓ.ም ዐረፉ። በምትካቸውም ሀዲስ ተክሌ የተባሉት አቡነ ዮሐንስ አዲሱ ሊቀ ጳጳስ ሆነው መስከረም 1 ቀን 1932 ዓ.ም ተመረጡ። በዚያው ቀን አቡነ ዮሐንስ ሌሎች 4 ጳጳሳትና አንድ ኤጲስ ቆጶስ ሾሙ። እነርሱም፤

1 / አቡነ ፊልጶስ- ኤጲስ ቆጶስ የአቡነ ዮሐንስ ጸሐፊ
2 / አቡነ ጎርጎርዮስ- የወሎ ጳጳስ
3 / አቡነ ማትያስ- የሸዋ ጳጳስ
4 / አቡነ አትናቴዎስ - የጎጃም ጳጳስ
5 / አቡነ ቄርሎስ - የኤርትራ ጳጳስ

አቡነ አብርሃም የሾሟቸው 6ቱ ጳጳሳት ከሥርዓት ውጭ ነው በማለት የግብጽ ቤተ ክርስቲያን አወገዘቻቸው። ይሁን እንጂ የተሾሙት ሥራቸውን ቀጠሉ።

ቤተ ክርስቲያናችንም እንደ ቀድሞ በአንድ ጳጳስ መመራት ትታ በራሱዋ ልጆች መመራት ከመጀመረች ጀምሮ መንፈሳዊ ተልዕኮዋም እየሰፋ ሲሄድ ዓላማዋን ከግቡ ለማድረስ በመስከረም 7 ቀን 1935 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ የቅድስት ሥላሴን ከፍተኛ መንፈሳዊ ኮሌጅ ተቋቋመ።
ወጣቶችም ከልጅነታቸው ጀምሮ በመንፈሳዊ ዕውቀት ተኮትኩተው እንዲያድጉ የወጣቶች መንፈሳዊ ማኅበራት ወይም በአሁኑ ወቅት የሰንበት ትምህርት የሚባለውን አቋቋመች። በዚህም በቀደምትነት የሚታወቁት በ1949 ዓ»ም የተመሠረቱት በምስካየ ኅዙናን መድኃኔዓለም ገዳም ሥር የሚገኘው የተምሮ ማስተማር ማኅበር በተለይ በአቅራቢያው ላሉት ለተፈሪ መኮንን እና ለእቴጌ መነን ተማሪዎች፤ የሃይማኖተ አበው ደግሞ ለዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች

ነበሩ። የነዚህንም አርአያ በመከተል ባሁኑ ወቅት በየክፍለ ሀገሩ በብዙው የኢትዮጵያ ግዛት በየአጥቢያው ከመ ቋቋም አልፈው በውጭው ዓለም ሁሉ የተለመደ ሆንዋል።

## የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከግብጽ ቤተክርስቲያን ነጻ መውጣት

ከነፃነት በኋላ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ በተለይ በዚያ ቀውጢ ወቅት የነበሩት ግብጻዊው አቡነ ቄርሎስ መንጋቸውን በትነው በግብ ጽ መቅረታቸው ቤተ ክርስቲያናችን በራሱዋ ልጆች መተዳደር አለባት የሚለውን ሐሳብ ላይ እንዲቀጥሉበት አደረጋቸው። ዐፄ ኃይለ ሥላሴም መልእክተኞችን ወደ ካይሮ በመላክ ያቀረቡት ጥያቄዎች የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ውግዘቷን ከአቡነ አ ብርሃም እንድታነሣ እና ቤተ ክርስቲያናችን ራሱዋን እንድትችል የሚል ነበር። ከረጅም ውይይት በኋላ በ1940 ላይ ስምም ነት ተደረሰ።

ይኸውም ኢትዮጵያዊ የሆነ የቤተ ክርስቲያኗ መሪ እንዲሾም ነገር ግን ይህ ተፈጻሚነት የሚኖረው በሕይወት የነበሩት አባ ቄርሎስ ካረፉ በኋላ እንዲሆን ተወሰነ። ይህም በኢትዮጵያ ዘንድ ተቀባይነት አገኘ። በዚህም መሠረት 5 አባቶች እንዲሾ ሙ በዚያው ዓመት ወደ ካይሮ ተልከው በቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን ሢመተ ጵጵስና ተፈጸመላቸው።
እነርሱም፤

1 / አቡነ ባስልዮስ- የሸዋ ጳጳስ
2 / አቡነ ሚካኤል- የጎንደር ጳጳስ
3 / አቡነ ቴዎፍሎስ- የሐረር ጳጳስ
4 / አቡነ ያዕቆብ- የወለጋ ጳጳስ
5 / አቡነ ጢሞቴዎስ- የሲዳሞ ጳጳስ

እነዚህ ጳጳሳት ተሹመው ሐምሌ 22 ቀን በአዲስ አባባ አውሮፕላን ማረፊያ እንደደረሱ ፣ በልዑል አልጋ ወራሽ አስፋ ወሰ ን፣ በታላላቅ ባለሥልጣናት በወታደራዊ ሰልፍ አቀባበል አድርገውላቸዋል። ከዚያም በሞተረኞች ታጅበው ወደ ቤተመንግሥ ት ሲሄዱ፣ ሕዝቡ በመንገድ ዳር በመሆን ደስታውን ይገልጽ ነበር። በቤተ መንግሥትም የአቀባበል ሥርዓት ከተከናወነ በኋ ላ አቡነ ባስልዮስ በሁሉም ስም ንግግር አድርገዋል። ንጉሠ ነገሥቱም የተሰማቸውን ደስታ ገልጸዋል።

በስምምነቱ መሠረት ግብጻዊው አቡነ ቄርሎስ በ1943 ዓ.ም ሲያርፉ አቡነ ባስልዮስ ጥር 1 ቀን 1943 ዓ.ም ወደ ካይሮ ሄደ ው ጥር 6 ቀን 1943 ዓ.ም በቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን በተደረገው ሥርዓት የኢትዮጵያ ሊቀጳጳስ ሆነው ተሾሙ።

ይህ ታላቅ ቀን ለኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ብቻ ሳይሆን ለሀገራችንም ክብር ትልቅ መልእክት ስለነበረው በሺህ የሚቆጠሩ ነዋሪዎች ወደ አውሮፕላን ማረፊያ በመሄድ የአቡነ ባስልዮስን መምጣት ይጠባበቁ ነበር። ብፁዕነታቸውን ለመቀበል ብፁዓ ን ጳጳሳት፣ ልዑል መኮንን መስፍኑ ሐረር፣ ሚኒስትሮችና መኳኳንት ሌሎችም ሊቃውንት በአውሮፕላን ማረፊያ በመገኘት በወታደራዊ ሥርዓት ተቀበሏቸው። ከዚያም በልዩ አውቶሞቢል ወደ ቤተ መንግሥት ሲሄዱ፣ በየመንገዱ ዳር ሕዝቡ ወጥ ቶ የደስታ ስሜቱን ይገልጽ ነበር። በቤተመንግሥትም ሲደርሱ ለክብራቸው 21 ጊዜ መድፍ ተተኮሰ። በመቀጠልም አቡነ ባ ስልዮስ ንግግር አድርገዋል። ግርማዊ ጃንሆይም በሳቸው ጊዜ ስለተፈጸመው ስለዚህ ታላቅ ውጤት እንዲህ ሲሉ ተናገሩ « ..............አሁን ግን እግዚአብሔር የሚሠራውን ሥራ በፈቀደ ጊዜ ስለሚፈጽም፤ ኢትዮጵያ አገራችን ነፃ ሕዝባችንና መንግሥ ታችን ራሱዋን የቻለች ቤተ ክርስቲያን እንዲኖራቸውና በዓለምም እንዲታወቅ አደረገ። ይህንንም በዘመናችን ስለተፈጸመል ን፤ እኛም ሕዝባችንም እኩል የምንኮራበት ነው። ያለፉት አባቶቻችን ይህን ተመኙ በተስፋም ተመለከቱት። በሃይማኖት የ ጸናች ተስፋ በዘመናችን ሲፈጸም ለማየት አበቃን።..............»

በዚያው ዓመት ነሐሴ 27 ቀን 1943 ዓ.ም ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ 3 ጳጳሳትን በቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ሾሙ። እነርሱም ፤

1 / አቡነ ጎርጎርዮስ- የከፋ ጠቅላይ ግዛት ጳጳስ
2 / አቡነ ታዴዎስ- የኢሉባቡር ጠቅላይ ግዛት ጳጳስ
3 / አቡነ ገብርኤል- የወሎ ጠቅላይ ግዛት ጳጳስ
4 / አቡነ ፊልጶስ- የኢየሩሳሌም ገዳማት ጳጳስ
5 / አቡነ ማርቆስ- የኤርትራ ጠቅላይ ግዛት ጳጳስ

በዕለቱም ለተሾሙት ጳጳሳት ታላቅ ግብዣ በቤተመንግሥት ተደርጐላቸዋል። ቤተ ክርስቲያንም የተፈጠረላትን ዕድል በመጠ ቀም የበለጠ ሐዋርያዊ ተልእኮዋን መፈጸም ቀጠለች። አሁንም የኢትዮጵያ ፍላጎት ከግብጽ ነፃ ወጥቶ ራስን መቻል ስለነበ ረ በአጋጣሚ ፓትርያርክ ዮሳብ በ1948 ሲያርፉ ፓትርያርክን ስለመምረጥ በተነሳው አለመግባባት ኢትዮጵያ ፓትርያርክ ስለመ ምረጥ በሚደረገው ጉባኤ እንደማትሳተፍና በበዓለ ሢመቱ ላይም እንደማትገኝ አስታወቀች። ነገር ግን ተጠባባቂው ግብጻዊ

ው አቡነ አትናቴዎስ በሚያዚያ ወር 1950 ዓ.ም ለንጉሠ ነገሥቱ በጻፉት ደብዳቤ ያለ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንና ያለ ለንጉሠ ነገሥቷ ተሳትፎ ምርጫው እንደማይካሄድ ገለጡ።ንጉሠ ነገሥቱም በደጃዝማች አሥራተ ካሳ የሚመራ 5 ልዑካን ያሉበት ቡድን ላኩ።

እነርሱም፤

1 / አቡነ ቴዎፍሎስ
2 / አቡነ ሉቃስ
3 / ብላታ መርስዔ ሀዘን ወልደ ቂርቆስ
4 / ደጃዝማች መኮንን ደስታ ናቸው።

መልእክተኞቹም የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን መብት በተመለከተ ብዙ ከተወያዩ በኋላ፣ በሐምሌ ወር 1950 የፕሮቶኮል ስምምነት ፈረሙ። የሆኖ ሆኖ ስምምነቱን የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ይፋ እንድታደርግ ብትስማማም ሆን ብላ አዘገየችው። በመጨረሻም በታኅሣሥ ወር አቡነ አትናቴዎስ በጻፉት ደብዳቤ እንዳመለከቱት በሐምሌ ወር 1950 የተፈረመውን የፕሮቶኮል ውሳኔ አጥፊው የግብጹ ፓትርያርክ ምርጫ በቀደመው ሕግ እንደሚካሄድ ገለጡ። ይህ መልእክት ደግሞ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ያሳዘነ በመሆኑ፣ ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ በየካቲት 21 ቀን1951 ዓ.ም ለአቡነ አትናቴዎስ በጻፉት ደብዳቤ ላይ፣ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መብት የማይከበር ከሆነ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከግብጽ ተነጥላ እንደምትቀጥል አስታወቁ። ወዲያው በሚያዚያ ወር የግብጽ ቤተክርስቲያን ኢትዮጵያውያን ባልተገኙበት ፓትርያርካቸውን መረጡ። አቡነ አትናቴዎስም በፓትርያርኩ ሢመተ ሥርዓት ላይ ንጉሠ ነገሥቱ እንዲገኙ ጋበዟቸው። ነገር ግን የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ወክሎ ማንም አልተገኘም። ለ1600 ዓመታት በሁለቱ ቤተ ክርስቲያናት መኻከል የነበረው ግንኙነት ከመቼውም ጊዜ የበለጠ አደጋ ላይ ወደቀ።

በግንቦት ወር መጨረሻ ላይ፣ አዲሱ ፓትርያርክ አቡነ ቄርሎስ ሳድሳዊ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ራሱዋን ስለምትችልበት ሁኔታ ለመወያየት ወደ አዲስ አባባ መልእክተኞችን ላኩ። ንጉሠ ነገሥቱም ሐሳቡን ተቀብለው በዚያው ወር መልእክተኞች ወደ ካይሮ ላኩ። በኢትዮጵያ በኩል የተላኩት መልእክተኞች ደጃዝማች አሥራተ ካሣ ፣አቡነ ቴዎፍሎስ፣ ብላታ መርስዔ ሀዘን ወልደ ቂርቆስ ናቸው። ከአምስት ቀን ውይይት በኋላ ስምምነት ላይ ተደርሶ ፕሮቶኮል ተፈረመ። በዚህም ፕሮቶኮል የተጠቃለለውና ዋና የነበረው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የራሱዋ ፓትርያርክ እንዲኖራት የሚል ነበር። በዚህም መሠረት ሰኔ 21 ቀን 1951 ዓ.ም ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ በመንበረ ቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን ንጉሠ ነገሥቱ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ በተገኙበት የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ሆነው ተሾሙ። ለዚህ ትልቅ ቀን ፍጹም ቅንነት ያሳዩትና ሁለቱ ቤተ ክርስቲያኖች ተካረው እንዳይለያዩ ትልቅ አስተዋጽኦ ያደረጉት ፓትርያርክ ቄርሎስ ናቸው። ለዚህም ከፍ ያለ ምሥጋና ይገባቸዋል። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንም ለ1621 ዓመታት በግብጽ ቤተ ክርስቲያን ሥር ከቆየች በኋላ ነፃ ወጣች። ከግብጽ ተሹመው ሲመለሱ ብፁዕነታቸውን ለመቀበል ብፁዓን ጳጳሳት፣ ንጉሣዊ ቤተሰቦች፣ ሚኒስትሮችና መኳኳንት ሌሎችም ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን በአውሮፕላን ማረፊያ በመገኘት በወታደራዊ ሥርዓት ተቀበሏቸው።

ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ ይህን ትልቅ ኃላፊነት ከተቀበሉ በኋላ ብዙ ሥራ የሠሩ ሲሆን፣ ከእነዚህም መኻከል የመንፈሳዊ ኮሌጅ በአዲስ አባባ እንዲከፈት፣ የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት ስብሰባ በአዲስ አባባ እንዲደረግና የዓለም አብያተ ክርስቲያን ማህበር ከመሠረቱት አንዷ ለመሆን በቃች። ይህን ፈጣን ዕድገት የተመለከተ አንድ የሀገራችን ሊቅ እንዲህ በማለት የገጠመው፣

ግብጽ እንደ እሥራኤል ሳይከተለን
የወሰድነው ልብስ ከርሱ ተውሰን
ለብሰንማ ቢሆን ዐጥፈን ደርበን
ስንኳን ካባይ ወዲህ ግዛታችንን
እንደ ስልቅ ሰዎች ጳጳስ እየሾምን
እንሰብካት ነበር ደቡብ አፍሪካን።

ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ የተሰጣቸውን ኃላፊነት በሚገባ እየተወጡ ሳለ በአደረባቸው ሕመም በ79 ዓመታቸው ጥቅምት 1962 ዐረፉ። ጸሎተ ፍትሐቱ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት፣ ንጉሠ ነገሥቱ ከቤተሰቦቻቸው እንዲሁም ከፍተኛባለሥልጣኖች በተገኙበት በመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ከደረሰ በኋላ፣ አስከሬናቸው በደብረ ሊባኖስ አርፏል።

ከብፁዕ አቡነ ባስልዮስ ቀጥሎ ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ በግንቦት 1 ቀን 1963 ዓ.ም ሁለተኛው ፓትርያርክ ሆነው በመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ተሾሙ። ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ ወደ ከፍተኛው የሥልጣን ደረጃ ከመውጣታቸው በፊት ጀምሮ፣ በእንደራሴነታቸው ለቤተ ክርስቲያኒቱ ዕድገት ከፍ ያለ አስተዋጽኦ ያደረጉ ሲሆን፣ ከእነዚህም ውስጥ የመንፈሳዊ ኮሌጅን በበላይ አስተዳደሪነት መምራት፤ ከላይ እንደተገለጸው ቤተ ክርስቲያናችን ከግብጽ ቤተክርስቲያን ነፃ እንድትሆን በተደረገው የድርድር ውይይት ላይ ተሳታፊ በመሆን፣ ብዙዎችን በማስተማርና ወደ ክርስትና እምነት እንዲመጡ በማድረግ

፣ በ1950 አካባቢ ላይ ቤተ ክርስቲያን ትስፋፋ ዘንድ የሐዋርያዊ ተልዕኮን መመሥረት፣ በሐረር ከሣቴ ብርሃን በሚል ስም የመንፈሳዊ ማህበር በማቋቋም ፣ የመንፈሳዊ ት/ቤቶችን በዚያው ክፍለ ሀገር በመክፈት ጠቃሚ አስተዋጽኦ አድርገዋል። በ ተለያዩ የዓለም አቀፍ ስብሰባዎች ላይ ቤተ ክርስቲያናችንን በመወከል ተገኝተዋል።

የኦሪየንታል አብያተ ክርስቲያናት ስብሰባ አዲስ አበባ ላይ በተካሄደ ጊዜ ጉባኤውን መርተዋል። እንዲሁም የኢትዮጵያ ኦር ቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በሰሜን አሜሪካ እና በእንግሊዝ እንድትስፋፋ አድርገዋል።

ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ ቤተ ክርስቲያን በሚገባ እንድትደራጅ፣ መንፈሳዊ ተልእኮዋን እንድትወጣና አገልጋይ ካህናቶቿም ላ ገልግሎታቸው ተመጣጣኝ ደሞዝ እንዲኖራቸው በማሰብ የሰበካ አስተዳደር ጉባኤን መሥርተው በቃለ ዓዋዲ እንድትመራ አድርገዋል። እንዲሁም ደግሞ የልማትና የተራድኦ እንቅስቃሴ በተቀላጠፈ ሁኔታ ይካሄድ ዘንድ የልማት ኮሚሽን በታኅሳስ 26 ቀን 1964 ዓ.ም እንዲቋቋም አደረጉ።

## <u>ከደርግ እስከ አሁን</u>

ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ የፓትርያርክነቱን ሥልጣን ከያዙ ከ5 ዓመታት በኋላ የዘውዱን ሥርዓት ያፈረሰው ወታደራዊው ደር ግ በየካቲት 9 ቀን 1968 ከሥልጣን አውርዶ በእስር እንዲቆዩ ካደረገ በኋላ፣ በምትካቸው አቡነ ተክለ ሃይማኖት እንዲመ ረጡ አድርጓል። ደርግ ብፁዕነታቸውን በእስር ቤት ሲያሰቃያቸው ቆይቶ ሐምሌ 1971 ዓ.ም ወደ ራስ አሥራተ ካሳ ግቢ በ መውሰድ በልዩ ነፍሰ ገዳይ ኮማንዶዎች በአሰቃቂ ሁኔታ አንገታቸውን አሳንቆ ገድሎ ከግቢው ውስጥ ባለ ጉድጓድ ውስጥ አስከሬናቸውን አስጥሎታል። በመጨረሻም ከ13 ዓመት በኋላ የብዙኃን ኢትዮጵያውያን ደም ያፈሰሰው ደርግ ተንኮታኩቶ ሲወድቅ ፤ ይህን የጭካኔ ተግባር ባዩ ሰዎች ጠቋሚነት ዐፅማቸው ከዚያ ወጥቶ በገዛ ገንዘባቸው በአሠሩት በጐፋ መካነ ሕ ያዋን ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ዐርፏል።

ጊዜያዊው ወታደራዊው ደርግ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ያለ አግባብ በቁጥጥር ሥር ካዋለ በኋላ፣ መሳሪያው አድርጎ ሊጠቀምባቸው ያስመረጠው ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ነበሩ። ምናልባት በአስተዳደር ችሎታቸው መጀመሪያ ላይ ድክመት ቢያሳዩም ፍጹም ፈሪሀ እግዚአብሔር የነበራቸው፣ ለዚህ ዓለም ድሎት ደንታ የሌላቸው ነበሩ። ውሎ አድሮ ግን ሁኔታውን እየተረዱ ሲመጡ በመንግሥትና በሳቸው መኻከል አለመግባባት ተፈጥሮ ነበረ።

ይህ በእንዲህ እያለ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በድንገት ይታመሙና ያርፋሉ። በዚህም ጊዜ ደርግ፣ የጎንደሩን ሊቀ ጳጳስ አቡነ መርቆሬዎስን፣ 4ኛው ፓትርያርክ በማድረግ እንዲሾሙ አደረገ። መንግሥት በተለወጠ ቁጥር በሥልጣን ላይ የሚወጣው መንግሥት የሚስማማውን ፓትርያርክ ማስቀመጥ እየተለመደ የመጣ ባሕል ይመስል፤ ወያኔ አዲስ አባባ ሲገባ አቡነ መርቆ ሬዎስ በሕመም የተነሳ ሥልጣናቸውን ለቀዋል በማለት መንበሩን እንዲያስረክቡ ተደርገዋል።

እንደተለመደው ፓትርያርክ ለማስመረጥ ዝግጅት ሲጀመር በአሜሪካ ከነበሩ ጳጳሳት መኻከል አንዱ ለመንበሩ ራሳቸውን ለማዘጋጀት ወደ አዲስ አባባ ብቅ አሉ። አወዛጋቢ በሆነው የምርጫ ሥርዓትም እኝሁ አቡነ ጳውሎስ አሸነፉ ተብሎ ታወ ጀ። አባ ጳውሎስም በትረ ሥልጣኑን የጨበጡት፣ ለእሳቸው ብቻ እንዲመጥን ሆኖ በቀረበው የምርጫ መመዘኛ ካባ ላንቃ ለብሰው መሆኑ ያን ጊዜውኑ ታውቋል።

በተለይ በአሁኑ ወቅት ተደገግሞ የሚነሳው ጥያቄ ፓትርያርክ እያለ እንዴት ሌላ ፓትርያርክ ይሾማል የሚለው ነው።ይህ ስ ህተት የተጀመረው በአቡነ ተክለ ሃይማኖት ጊዜ ነው። አቡነ ተክለ ሃይማኖት ሲሾሙ አቡነ ቴዎፍሎስ በእስር ላይ ነበሩ። በወቅቱ የነበረው ሲኖዶስ አቡነ ቴዎፍሎስ ከእስር እንዲፈቱ መንግሥትን መጠየቅ ሲገባው፤ ከነበሩት የሲኖዶስ አባላት መካከል አስራ አንድ በሚሆኑት ሊቃነ ጳጳሳት በየካቲት 18 ቀን 1968 ዓ.ም መዝገብ ቁጥር ፋ18/68/77 ተፈርሞ የቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ ተብሎ «ደርግ ለቤተ ክርስቲያን ዕድገት ሲል በአቡነ ቴዎፍሎስ ላይ የወሰደውን እርምጃ ደግፈናል» ተብሎ ለደርግ የተጻፈው ደብዳቤ ለሦስተኛው ፓትርያርክ ምርጫ ዝግጅት መንገድ ከፈተ። አቡነ ተክለ ሃይማኖት ከተሾሙ በኋ ላ በመጀመሪያ ላይ በሐሰት ወንጀሎ በእስር ቤት የጣላቸውን አባት መፍታት የበለጠ ችግር እንደሚያመጣ የተረዳው ደርግ የፈጸመውን ስሕተት ለመሸፈን እንደተለመደው የሌላ ንጹህ ሰው (አባት) ሕይወትን አጥፍቷል።

ለውጥ በመጣ ቁጥር በቤተ ክህነቱ በኩል የሚታየው አሳዛኝ ባሕርይ ለዘመናት የቆየችዋን ታላቋን ታሪካዊ ቤተ ክርስቲያናች ንን በሀገርና በውጭው ዓለም ትዝብት ላይ ጥሏታል። በዲሞክራቲክ መንገድ በሕዝብ ዘንድ የተመረጠ መንግሥት ሀገሪቷን እስካልመራ ድረስ፤ በጠመንጃ ኃይል ሥልጣን ላይ የሚፈናጠጡ መሪዎች እስካሉ ድረስ በቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ውስ ጥ ጣልቃ መግባታቸው የማይቀር ነው። ይህን የአምባገነን መሪዎች ጣልቃ ገብነት ማሰቆም የሚቻለው ደግሞ አባቶች አን ድ ሲሆኑና እንደ ቤተ ክርስቲያናችን እምነትና ሥርዓት ሕይወታቸውን ሲመሩና ቤተ ክርስቲያንም በገንዘብ ደረጃ ራሷን ች

ላ ስትጓዝ ነው። እዚህ ላይ የግብጽ ቤተ ክርስቲያን በሳዳት ጊዜ የገጠማትን ችግርና እንዴት እንዳሳለፈችው ማንሳት ለኛ ትምህርት ሊሆን ይችላል። ፕሬዚዳንት ሳዳት ግብጽን በሚመራበት ወቅት የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ የነበሩትን አቡነ ሺኖዳ ከሥልጣናቸው እንዲወርዱ አድርጎ በግዞት በበረሃ እንዲቀመጡ ባደረገበት ወቅት፤ ሌላ ፓትርያርክ እንዲሾሙ ሲኖዶሱ ላይ ግፊት አድረጎ ነበር። የሆኖ ሆኖ ሲኖዶሱ አቡነ ሺኖዳ በሕይወት እስካሉ ድረስ ሌላ አይሾምም ብሎ ፕሬዚዳንት ሙባረክ ሥልጣን ይዞ አቡነ ሺኖዳ ከተጋዙበት ተመልሰው መንበረ ፓትርክናውን እስኪይዙ ድረስ በሲኖዶስ ሲተዳደሩ ቆይተዋል። እኛም እንግዲህ እንደ ግብጽ ቤተ ክርስቲያን አባቶች፤ የኛም አባቶች በወቅቱ አቡነ ቴዎፍሎስ ይለቀቁ ልን ሌላም አባት አንሾምም ቢሉ ኖሮ ደርግም የንጹሕ ሰው ደም ባላፈሰሰ ነበር ፤ ቤተ ክርስቲያናችንም በአስተዳደር በኩል እንዲህ ምስቅልቅሏ ባልወጣ ነበር።

በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ያሉት ፓትርያርክ ሥልጣን ከያዙበት ቀን ጀምሮ የወያኔ መንግሥት እስካለ ድረስ በሚል ይመስላል ምግባራቸው ብልሹ የሆነ ፤ ቀኖና ቤተ ክርስቲያኑንም እያፈረሱ ከሚፈጽሟቸው ተግባራት አልፈው ስውር ታጣቂዎችቸው፣ አንጋች አጃቢዎቻቸው በጠራራ ፀሐይ በቤተ እግዚአብሔር አደባባይ ንጹህ ደም እንዲፈስ አድርገዋል። ከማስገደልም አልፍው የሟች ባህታዊን አስከሬን በየትኛውም ቤተ ክርስቲያን እንዳይቀበር ከልክለዋል። በአንጻሩ የሮማ ካቶሊክ ፓፓ የነበሩት ሕይወታቸውን ለማጥፋት ተኩሶ ያቆሰላቸውን የቱርክ ዜጋ ይቅር ከማለት አልፈው እስር ቤቱ ድረስ በመሄድ ጠይቀውታል። ታዲያ የክርስትና አንዱ መመሪያ የሆነው ጠላትን ሁሉ መውደድ እንዳለብን የሚያስተምረን ሃይማኖታችን በራሷ መሪ ሲጣስ ምን ይባላል?

እንዲህ ያለ ይሉኝታ ያለ ኀፍረት የሚፈጽሙአቸውን (ዘረኝነታቸውን፣ ኀጠኝነታቸውን ፣ አልጠግብ ባይነታቸውን፣ ተድላ ደስታ ወዳድነታቸው፣ ቂመኛነታቸውን፣ በቀለኛነታቸውን) ያየ፤ እንኳንስ ከአንድ የቤተ ክርስቲያን አባት ይቅርና፣ ፈሪሀ እግዚአብሔር ካገበረው ከአንድ ጥሩ ክርስቲያን የማይጠበቅ መሆኑን መገንዘብ አያዳግትም።

በሀገር ቤት በአባ ጳውሎስና በመሰሎቻቸው ፍዳዋን እያየች ያለችው ቤተ ክርስቲያናችን እዚያ የሚሠራው በደል አልበቃ ብሏት፤ አባ ጳውሎስ መጠቀሚያ ያደረጓቸውን ሰዎች ወደ ውጨው ዓለም በመላክ ምዕመናንን በመከፋፈል፤ በሰላም የሚገለገሉ ቤተ ክርስቲያናትን በማወክ እመዘጋት ደረጃ ላይ እንዲደርሱ (ለምሳሌ በአውስትራሊያ ሜልበርን)፤ አሁን በቅርቡ ደግሞ ወደ እንግሊዝ ጳጳስ በመላክ የምእመናንን ሰላም የሚነሱ ሆነዋል። በአሜሪካ የሚገኙትንም ለመከፋፈል አገልጋይ ካህናትን ወስዶ ጳጳስ አድርጎ ሾሞ በመላክ፣ ሌላውን ደግሞ ወደ ሀገር ቤት ከመጣችሁ ወይም ደግሞ ያላችሁበትን ቤተ ክርስቲያን በኢትዮጵያ ሥር እንዲሆን ካደረጋችሁ የተለያየ ነገር እናደርግላችኋለን በማለት በረቀቀ መንገድ ምዕመናን የበለጠ እንዲከፋፈሉ እያደረጉ ነው። ይህ በእንዲህ እያለ በጥር ወር በአሜሪካ አቡነ መርቆሬዎስ 13 ጳጳሳትን ሾመዋል። እነዚህን ጳጳሳት መሾም ያስፈለገበት ምክንያት ተብሎ የተሰጠው ቤተ ክርስቲያን በውጭው ዓለም እየተስፋፋችና ያሉትም አባቶች ሁሉን ለማዳረስ ስላልተቻለ ነው የሚል ነው። የሆኖ ሆኖ ቤተ ክርስቲያናችን ከዚህ ቀጥሎ ወደየት እንደምታመራ ለመተንበይም ሆነ ለመገመት አስቸጋሪ የሆነበት ወቅት ነው።

ይህ የተመሰቃቀለ ጊዜ አልፎ ቤተ ክርስቲያናችን በአንድነት፤ ሰላም በሀገራችን ሰፍኖ ሕዝቦቿ በፍቅር፤ በአንድነት የሚኖርባት ኢትዮጵያ እንድትመጣ በዘመን የቀደሙ አባቶቻችን ጸሎት አይለየን።

## በአዲስ አበባ የኦሪየንታል ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ጉባኤ

ይህ ጉባኤ የተካሄደው እንደ አውሮፓውያኑ የዘመን አቆጣጠር ጥር 1965 አዲስ አበባ በሚገኘው የአፍሪቃ አዳራሽ ነው። በዚህ ስብሰባ የአምስቱ እህትማማች ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያናት ማለትም፤ የኢትዮጵያ ፣ የግብጽ፣ የሶርያ ፣ የአርመን ፣ የሕንድ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከመልእክተኞቻቸው ጋር በመገኘት ተሳትፈዋል።ይህንን ጉባኤ ልዩ የሚያደርገው እነዚህ እህትማማች ቤተክርስቲያናት ለመጨረሻ ጊዜ የተሰበሰቡት በ5ኛው ክፍለ ዘመን (431 ዓ.ም) በኤፌሶን ነው። ይህ ከ15 ክፍለ ዘመናት በኋላ የተካሄደው ጉባኤ ዓላማው በእነዚህ ቤተ ክርስቲያኖች መሐከል የበለጠ መቀራረብ እንዲኖር፣ ሐዋርያዊ ተልእኮን በዓለም ማሰራጨት የሚቻልበትን መንገድ ለመወያየትና ስለ እምነታቸው ጥልቅ የሆነ ሃይማኖታዊ ውይይት ለማድረግ ነው። እንደ አውሮፓውያኑ አቈጣጠር በግንቦት 18 ቀን 1964 ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ለእነዚህ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያናት በኢትዮጵያ ርዕሰ ከተማ በአዲስ አበባ ሊያዘጋጁት ባሰቡት ጉባኤ ላይ እንዲገኙ የጥሪ ግብዣ አስተላለፉ። እነዚህም ቤተ ክርስቲያናት በጉባኤው ለመገኘት ፈቃደኝነታቸውን በመግለጻቸው ጉባኤውን የሚያዘጋጅ አንድ ኮሚቴ ተቋቋመ።የኮሚቴውም አባላት፤

- ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ (የሐረር ሊቀ ጳጳስ) የኮሚቴው ሊቀ መንበር

- ባላምባራስ ማህተመ ሥላሴ (የሕዝብ ሥራ ምኒስትር) የአቀባበልና ዝግጅቱ መሪ
- አቶ አበበ ረታ(የጤና ጥበቃ ምኒስትር) ጸሐፊ በመሆን ተሰየሙ።

ይህ ኮሚቴ ከሌሎቹ የቤተ ክርስቲያናት መሪዎች ጋር በመሆን ለጉባኤው መነጋገሪያ አጀንዳዎችን ነደፈ። በዚህም መሠረት ጉባኤው እንደ አውሮፓውያኑ የዘመን አቈጣጠር ከጥር 7 እስከ 14 ቀን 1965 ከእነዚህ እህትማማች ቤተ ክርስቲያን የመጡ የሃይማኖት ሊቃውንት የተሰበሰቡ ሲሆን ጉባኤውን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ወክለው የተገኙት በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ሊቀጳጳስ የነበሩት አቡነ ፊልጶስ በጸሎት ከፍተዋል። በዝግ በር በተካሄደው በዚህ ጉባኤ ቀጣዩን ጉባኤ የሚወያይበትን አጀንዳዎች ተወያይቶ አቅርቧል፤ ይኸውም

- የሰለጠነው ዓለምና ቤተ ክርስቲያኖቻችን
- ስለ ሃይማኖታዊ ትምህርት ትብብር
- ስብከተ ወንጌልን ስለማስፋፋት
- ስለ እርስ በርስ ግንኙነት
- የጠበቀ ቋሚ ግንኙነት እንዲኖር አንድ አካል ስለ መመሥረት
- ስለ ዓለም ሰላምና ፍትሕ መግለጫ ማውጣት የሚሉት ነበሩ።

እንደ አውሮፓውያኑ የዘመን አቈጣጠር ከጥር 15 እስከ 21 ቀን 1965 የ5ቱ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከመልእክተኞቻቸው ጋር በመገኘት ስብሰባውን ተካፍለዋል። ስብሰባው በዐፄ ኃይለ ሥላሴ የእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር ካደረጉ በኋላ በማከታተል የሶርያው ቤተክርስቲያን መሪ አቡነ ሞራን ማር ኢግናቲዎስ ያዕቆብ 3ኛ እና የአርመን ቤተ ክርስቲያን ተወካይ አቡነ ቫስከን 1ኛ ንግግር አድርገዋል። ጉባኤውን በየቀኑ ሲካሄድ ሰንብቶ ጥር 21 ቀን በዐፄ ኃይለ ሥላሴና በ5ቱ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች የመዝጊያ ንግግር ተፍጽሟል። በዕለቱም ዐፄ ኃይለ ሥላሴ «የሃይማኖት ጠባቂ» የሚለው ቅጥያ ተሰጥቷቸዋል። ጉባኤው የጠበቀ ቋሚ ግንኙነት እንዲኖር በወሰነው መሠረት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጊዜያዊ ኮሚቴ በአቶ ሰይፉ መታፈሪያ ጸሐፊነት አዲስ አበባ ላይ አቋቁማለች። ስለዚህ የተወጠነው የጉባኤው ዓላማ ቀጣይነቱ የተረጋገጠ ሆኗል።

**በእደ ማርያም እጅጉ ረታ** (January 2004)

## <u>ዋቢ መጻሕፍት</u>


1/ ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ፤ <u>ዋዜማ፤</u> 1921።
2/ የጋዜጣና ማስታወቂያ መሥሪያ ቤት ያሳተመው፤<u>የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ዕድገትና ነፃነት በኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት</u>፤ ጥቅምት 15 ቀን 1944።
3/ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፤ <u>የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐፄ ይኩኖ አምላክ እስከ ዐፄ ልብነ ድንግል</u> ፤ 1951።
4/ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፤ <u>የግራኝ አህመድ ወረራ፤</u> 1966።
5/ አባ ጎርጎርዮስ <u>የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ፤</u> 1974።
6/ ከአበራ ጀምበሬ፤ <u>የእስር ቤቱ አበሳ በታላቁ ቤተ መንግሥት፤</u> 1985።
7/ አቡነ ጳውሎስ <u>የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ አጭር የሕይወት ታሪክ፤</u> 1987
8/ Silvia Punkhurst, <u>Ethiopia A cultural History</u>, 1955.
9/ Edited by the interim secretariat , <u>The Oriental Orthodox churches Addis Ababa Conference January</u>, 1965.
10/ A publication of the Ethiopian Orthodox Church Addis Ababa, <u>The Church of Ethiopia</u>, 1970.
11 / The Ethiopian Orthodox Church mission Addis Ababa, <u>The Ethiopian Orthodox Church</u>, 1970.
12 / Yolande Mara, <u>The Church of Ethiopia (The national church in the making)</u>, 1972.
13 / Sergew Hable selassie (Associate Professor), <u>Ancient and Medieval Ethiopian History to 1270</u>, 1972.
14 / Taddesse Tamrat (Professor), Church and State 1270-1527, 1972.
15/ Sven Rubenson, The Survival Of Ethiopian Independence, 1991.